# የታላቁ “ከበሮ” አፈታሪክ

በገ/ኢ.ጐርፉ

ትርጉም፡- በአንደኛ ተሸላሚው በዓብይ ጣሰው

(tassewabiy2@gmail.com)

(0932 097070)

ለሰናይ ግርማ ማስታወሻ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትርጉም ውድድር የቀረበ



ሰናይ ግርማ

1988 – 2014

# የታላቁ “ከበሮ” አፈ ታሪክ (ነጋሪቱ)

*መግቢያ*

*ይህ የኢትዮጲያዊው ከበሮ፣ የነጋሪቱ አፈ ታሪክ ነው! በጥንት ጊዜ በኢትዮጲያ ስለተሠራ እጅግ ግዙፍና እጅግ ግዙፍ ከመሆኑ የተነሳ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ለማንቀሳቀስ አራት ፈረሶች የሚጎትቱት ሠረገላ ስለሚያስፈልገው ከበሮ ታሪክ ተነግሮናል፡፡ ከበሮ መቺው ከበሮውን ሲነርተው፣ አፈ ታሪኩ እንደሚለው እስከ ሰማንያ ኪሎ ሜትሮች ርቀት ድረስ ይሰማ ነበር፡፡ ይህ የዚህ ከበሮ ታሪክ ነው፡፡*

*ይህን አፈ ታሪክ መጀመሪያ ልጅ እያለሁ ከዚያ በጉብልነት ጊዜዬ ታሪኩን ከነገሩኝ ሦስት የተለያዩ ተራኪዎች ተቀብያለሁ፡፡ ሁለቱ ወንዶች እና የቤተሰቤ አባላት ሲሆኑ በልጅነቴ ታሪኩን የነገሩኝ እነርሱ ነበሩ፡፡ ሦስተኛዋ ቢደግሁበት መንደር የምትገኝ አዛውንት ሴት ስትሆን፣ ምንም ዓይነት ዝምድና ባይኖረንም የዓስራ አራት ዓመት ጎረምሳ እያለሁ ድሮ የማውቀውን ታሪክ ደግሞ ተርካልኛለች፡፡ የእያንዳንዳቸው አተራረክ ዘዬ ቢለያይም ታሪኩ ግን አንድ ነበር፡፡ ከዋናው ታሪክ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ሳልዛነፍ፣ በተቻለኝ መጠን ታማኝ ሆኜ እተርካሁ፡፡ በአተራረኩ ላይ የተወሰኑ ለውጦች ካሉ ለአንባቢ አሳውቃለሁ፡፡*

*ገ/ኢ.ጐርፉ፣ ሎስ አንጀለስ (1989)*

1

## ከበሮው

ይህ “ነጋሪት” ተራ የመንደር ባለሙያ ወይም ማንም ከበሮ ሠሪ ሊሠራው የሚችለው አይደለም፡፡ በንጉሥ ትእዛዝ የተሠራ ልዩ ከበሮ ነበር፡፡ የትኛው ንጉሥ ከበሮው እንዲሠራ እንዳዘዘ በጊዜያት ንብርብር ውስጥ ጠፍቶ አይታወቅም፡፡ ነገር ግን ከበሮው በንጉሥ ትእዛዝ እንደተሠራ፣ ተሠርቶም ሲያልቅ በቤተ መንግሥት ውስጥ እንደተቀመጠ፣ ለንጉሡም በርካታ አገልግሎት ሲሰጠው እንደነበር፤ ከዚያም ከአንዱ ንጉሥ ወደ ሌላው፣ ከትውልድም ወደ ትውልድ እየተላለፈ ለብዙ ዘመናት እንደቆየ ታውቋል፡፡

**መጀመሪያ መጠኑ፡** አንድ ክንድ የአንድ ሰው ከመሃል ጣቱ እስከ እጅ መታጠፊያው ድረስ ያለው ርቀት ሆኖ- በግምት ስድሳ ሳንቲ ሜትር ይሆናል- ከበሮው ከፊት ለፊቱ ወይም ዋናው አፉ አራት ክንድ ይሰፋል፡፡ ከሁለት ሜትሮች በላይ ማለት ነው፡፡ ትንሹ አፉ ወይም የኋለኛው ክፍሉ ሁለት ከግማሽ ክንድ- አንድ ሜትር ከተኩል ግድም ይሆናል፡፡ በሁለቱ አፎቹ መካከል ያለው ርቀት ደግሞ ሰባት ክንድ ወይም ከአራት ሜትሮች በላይ ይረዝማል፡፡ እንደው በደፈናው የሰማይ ስባሪ ያህላል ማለት ይቻላል፡፡ በቅርብ ጊዜያት ውስጥ እንኳ አምሳያ ያልተገኘለት ከበሮ ነበር፡፡

አገልግሎት ላይ የሚውለው ንጉሡ በሚያከብራቸው የተለያዩ በዓላትና አጋጣሚዎች፣ አዲስ ዓመት መግባቱን ለማበሰር፣ ልዩ መልእክቶችን ለማስተላለፍ፣ ምርት እዲሰበስቡ ሕዝቡን ለመጥራት፣ ለጦርነት ከራሶቹና አማካሪዎቹ ጋር ለመወያየት፣ “ክተት ሰራዊት” ለማወጅ… ወ.ዘ.ተ ነበር፡፡ ምናልባት ዛሬ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ስልኮች እጅግ ኋላ ቀር በሚባሉ ቦታዎች እንኳ ሳይቀር በሰፊው በገቡበት በአሁኑ ዘመን ለምንኖር ሰዎች የከበሮውን ጥቅም በውል ላንረዳው

እንችላለን፡፡ ነገር ግን ኣፈ ቀላጤ (ኣፈ ቃል ሃፄ፣ ቀጥተኛ ፍቺው የንጉሡ ኣፍ ቃል) በመባል የሚታወቀውን የንጉሡን ቃል የሚያደርሱ መልእክተኞች በእግር ወይም በፈረስ እየጋለቡ መጓዝ ግድ በሚሆንባቸው፣ የተስተካከለ መንገድ ባልነበረበት፣ ቅርብ የሚባሉ ቦታዎች እንኳ ለመድረስ ሁለት ቀናት ኣሊያም ሳምንት ይወስድ በነበረበት ዘመን፣ በተለይም በዝናም ወራት ብዙ ሳምንታት በሚፈጅበት በዚያን ጊዜ በረዥም ርቀት የሚሰማ ከበሮ ኣስፈላጊነቱ ወሳኝ ነበር፡፡ ከኣሁኑ ዘመን የቴክኖሎጂ ውጤት ከሆነው የሞባይል ስልክ ጋር የሚመጣጠን ነው፡፡

**2**

**ባለሙያዎችን መረጣ፡** ኣፈ ታሪኩ እንደሚለው ንጉሡ በግዛቱ የሚገኙትን ከበሮ ሠሪ ባለሙያዎችን ድግስ ደግሶ ጠራቸው፡፡ በድግሱም ንጉሡ እያንዳንዱን ባለሙያ ኣዘውትረው ስለሚሠሩት የከበሮ መጠንና ሊሠሩት ስለሚችሉት ታላቅ የከበሮ መጠን ጠየቃቸው፡፡ ኣብዛኛዎቹ በዚያን ግዜያት ለኣብያተ ክርስቲያናት ከሚሠሩት ከበሮዎች የበለጠ መሥራት እንደማይቻል ተናገሩ፡፡ ከነዚህ ከበሮዎች ግዙፍ የሚባለው፣ ምንም እንኳ ትልቅና ከባድ ቢሆንም ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች በቀላሉ የሚያነሱት ነበር፡፡ እንዲያውም ኣብዛኛዎቹ ረዘም ያለ ጉልበታም ሰው የሚያነሳቸው ነበሩ፡፡ ነገር ግን ከተጋበዙት ከበሮ ሠሪዎች መካከል ሁለት ባለሙያዎች ለንጉሡ ዋናው ወሳኝ ነገር የዛፉ ውፍረት እና የቆዳው ስፋት ነው፤ እነዚህን ሁለት ነገሮች ናቸው የከበሮውን መጠን የሚወስኑት ሲሉ ኣስረዱት፡፡ እነዚህን ገደቦች ማለፍ ከተቻለ ጃንሆይ የሚፈልጉትን መጠን ከበሮ ሊሠሩ እንደሚችሉ ኣረጋገጡ፡፡

የባለሙያዎቹ ምላሽ ንጉሡን ኣስደሰተው፡፡ የተቀሩትን ከበሮ ሠሪዎች ኣሰናብቶ እነዚህን ሁለቱን መረጣቸው፡፡ ከዚያ ጃንሆይ ሁለቱ ከበሮ ሠሪዎች ተባብረው ከዚያ በፊት ተሠርቶ የማይታወቅ ትልቅና ኣስገምጋሚ ከበሮ እንዲሠሩለት ጠየቃቸው፡፡ እነርሱም ተስማሙ፤ በዚህም በግዛቱ ውስጥ ሊገኝ የሚችልን ወፍራም ዛፍ ማሰስ ተጀመረ፡፡ ለንጉሡ የሚመጥን ዛፍ ለማግኘት ኣሳሾች በየኣቅጣጫው ተላኩ፡፡ በዚያን ጊዜያት ሰዎች የሚጓዙት በእግር፣ በፈረስ፣ በበቅሎ፣ በኣህያ እና በግመል ስለነበርና ከነዚህ ውጭ ሌላ መጓጓዣ ስላልነበር፣ ከትግራይ ተነስቶ ወደ ንግሥናው ግዛት ደቡብ ጫፍ ለመድረሥ ስድስት ወራትን በደንብ አድርጎ ይወስድ ነበር፡፡



የአሳሽ ግብረ ኃይሉ ኣለቃ የሚፈለገው ዛፍ እንደተገኘ ሲያሳውቅ ሁለት ዓመታት ፈጅቶ ነበር፡፡ በግዛቱ ደቡባዊ ክልል፣ ከጊቤ ወንዝ በስተምዕራብ ኣቅጣጫ የሦስት ቀናት ጉዞ ተሄዶ ከሚገኝ ቦታ ነበር የዲማው ዛፍ የተገኘው፡፡ ዛፉን ሙሉ ለሙሉ ለማቀፍ ኣምስት ሰዎች እጆቻውን ሙሉ ለሙሉ ዘርግተው የመሃል ጣቶቻቸውን ማነካካት ያስፈልጋቸዋል ተብሏል፡፡ የኣንድ መካከለኛ ሰው የተዘረጉ እጆች ከመሃል ጣቱ ጫፍ እስከ ሌላኛው የመሃል ጣቱ ጫፍ ያለው ርዝመት በኣንድ ሜትር ተኩል እና በሩብ ጉዳይ ለሁለት መካከል ይሆናል ብለን ብንገምት፣ የዛፉ መጠነ ዙሪያ በሰባት ሜትር ከተኩል እና በዘጠኝ ሜትሮች መካከል፣ ኣጋማሽ ርቀቱ ደግሞ ወደ ሦስት ሜትሮች ይሆናል ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ዛፉ እንደ ሌሎች ምራጭ ዛፎች ሻካራና ጎባጣ ኣልነበረም፤ ለስላሳና በስትክክሉ የተከበበ ነበር፡፡ ይህ ዛፉን ለሚፈለገው ዓላማ ተመራጭ አድርጎታል፡፡

## 3

***ቅድመ ሥራ፡*** ዛፉን መቁረጥ አስቸጋሪ አልነበረም፡፡ ዓስር ሰዎች ቅርንጫፎቹን እና ሥሩን አስወግደው ለከበሮው መሥሪያ የሚያስፈልገውን ጉማጅ ለማዘጋጀት ሦስት ሳምንታት አስፈልጓቸዋል፡፡ ይህ ካለቀ በኋላ የግንዱ ጉማጅ ለሥራ ኣመች ወደ ሆነ ቦታ እንዴት ሊወስዱት እንደሚችሉ ብልሓት መፈለግ ነበረባቸው፡፡ ካጋጠሚቸው ተግዳሮቶች መሃከል ኣንደኛው ይህ ነበር፡፡ ግንዱን ለማጓጓዝ ዓይነታው መንገድ የግቤን ወንዝ ተፋሰስ ተከትሎ ግንዱን ውሃው ላይ እያንሳፈፉ መውሰድ እንደሆነ ተስማሙ፡፡ ወደ ወንዙ ለመድረስ ዓቀበት ቁልቁለት የሞላው የሦስት ቀናት ጉዞ ነበር፡፡ ግንዱን ሜዳው ላይ ማንከባለል፣ ዓቀበቱ ላይ መግፋት፣ ቁልቁለቱ ሲሆን መጎተት፤ ከወንዙ ለመድረስ በማንኛውንም ዓይነት መታገል ነበረባቸው፡፡ ከወደ ሁለት ወር ገደማ ከወንዙ ደረሱ፡፡ ከወንዙ ዳርና ዳር ዓስር ዓስር ፈረሶችን ወይም በቅሎዎችን ኣድርገው ግንዱን ወንዙ ውስጥ ከጨመሩት በኋላ በገመዶች ከእንስሶቹ ጋር ኣሰሩት፡፡ ጓዛቸው ወደ ሰሜን ኣቅጣጫ፣ የግቤ ወንዝ የሚፈሰው ደግሞ ደቡብ ኣቅጣጫ ነው፡፡ እንስሶቹ ግንዱን በተቃራኒው ኣቅጣጫ መጎተት ነበረባቸው ማለት ነው፡፡ ፏፏቴዎችንም ሽቅብ መውጣት ግድ ሆኖባቸው ነበር፡፡ ከስንት ውጣ ውረድ በኋላ ስድስት ወራት ሊሞላቸው ሲል ኣመቺ ከሆነ የወንዙ ሰሜናዊ ጫፍ ደረሱ፡፡ ግንዱን ከወንዙ ማውጣት ኣለባቸው፡፡ ለዚህ በግራና ቀኝ ካሉት ሃያ እንስሶች ሌላ ግንዱ የታሰረበትን ገመድ የሚጎትቱ ሓምሳ ተጨማሪ ሰው ኣስፈልጓል። በወንዙ ውስጥ በቆየባቸው ጊዜያት ግንዱ ውሃ ጠጥቶ ስለነበር ኣሁን እጅግ ከብዷል፡፡

ይሄኔ ነበር ንጉሡ ከበርካታ ዓስርት መኳንንቶች፣ ሁለት መቶ ጠባቂዎች፣ ወታደሮች፣ እግረኞችና ጋሻ ጃግሬዎች ጋር ወደ ኣንድ ሺሕ ሰው ኣስከትሎ ግንዱን ለመጀመሪያ ጊዜ ለማየት የመጣው፡፡ እንደሚባለው ንጉሡ ግንዱን ሲያይ በምርጫው ተደሰተ፡፡ ከዚያው ደማቅ ድግስ ተደገሰ፡፡ ንጉሡን ዓጅበው የመጡት ሊቀ ጳጳሱ፣ ቀሳውቅቱና እጨጌዎቹ በተራቸው ቡራኬና ጸሎት ኣደረሱ፣ ግንዱን ፀበል ረጩት፡፡ ብዙ ላሞችና በሬዎች ታርደው ትልቅ ግብዣ ተደረገ፡፡ በዚያ ሰዉ ለሦስት ቀናት ጨፈረ፣ ፈነጠዘ፡፡ ኣሁን ግንዱን ወደ ከበሮ የመለወጥ ከባዱ ሥራ መጀመር ይቻላል።

## 4

***ሥራው፡*** ብዙ ኣነስተኛ ደንኳኖች ተተከሉ፡፡ ሓምሳ ባለሙያዎች፣ ምግብ የሚያሰናዱ፣ የሚጠጣ የሚያቀርቡ፣ የማገዶ ዕንጨት የሚሰበስቡ መቶ ሓምሳ ወንድና ሴቶች፣ ሰፈሩንና ሠራተኞቹን የሚጠብቁ ንጉሡ የተዋቸው ሓምሳ የታጠቁ ወታደሮችን ኣካትቶ የሥራ ግብረ ኃይሉ ተደራጀ፡፡ ግንዱ ከሌላ የዲማ ዛፍ ጥላ ሥር ሆኖ ረጅሙና አስቸጋሪው የመፋቅና የመቦርቦር ሥራ ተጀመረ፡፡ የግንዱን የመሃለኛ ክፍል ቦርቡሮ ለማውጣት ብቻ ከሁለት ዓመት ከግማሽ በላይ ፈጀ፡፡ ቀስ ብለው በጥንቃቄ ሳይቸኩሉ ነበር የሚሠሩት፡፡ በመጨረሻ የመጠነ ዙሪያው ስፋት ስድስት ሳንቲ ሜትር የወፈረ፣ ሠፊኛው አፉ ሁለት ሜትር ከግማሽ ሊሞላው ምንም ያልቀረው፣ ቁመቱ ከአራት ሜትሮች በላይ የረዘመ፣ ትንሹ ኣፉ አንድ ሜትር ከግማሽ የሠፋ ያማረ፣ የተስተካከለ፣ የለሰለሰ ቀፎ ወጣ፡፡ ቀጥሎ ያለው ሥራ ሁለቱን አፎቹን በቆዳ ማልበስ ነበር፡፡

የየትኛውም ዓይነት የላም ወይም የበሬ ቆዳ፣ ምንም ቢሰፋ የከበሮውን ዋና ኣፍ ሊሸፍን እንደማይችል የታወቀው ገና በጠዋቱ ነበር፡፡ ንጉሡ በግዛቱ ካሉት ዝሆኖች ግዙፉን ገድለው ቆዳውን፣ የታፋዎቹን እንዲሁም የፊትና የኋላ እግሮቹን ዓጥንቶች እና ጥርሶቹን እንዲያመጡ ምርጥ ኣዳኞች ልኳል፡፡ ኣዳኞቹ ቆዳውን እንዳያበላሹ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ፣ በመሆኑም ዝሆኑን ከየት ቦታ መምታትና መውጋት እንዳለባቸው ጥብቅ ትእዛዝ ተሰጥቷቸዋል፡፡

ጭንቅላቱን፣ አሊያ ከሆዱ ሥር ገብተው መውጋት ነበር ያለባቸው፡፡ ቆዳውን መና ስለሚያስቀረው ልቡን ወይም ትከሻውን መውጋት አይቻልም፡፡ አብዛኛው አዳኝ ከሚታደነው እንስሳው ጎንና ጎን ሆኖ እንደ ልብና ሳንባ የመሳሰሉ ስስ ብልቶችን መውጋት ጥሩ ዘዴ መሆኑ ያውቃል፣ ግን ለዚህ ልዩ ግዳጅ ይህ ዘዴ አይፈቀድም፡፡ አደኑ የሚካሄደው የባሩድ ጥይት ወደ ኢትዮጲያ ከመግባቱ በፊት አዳኞች ጦሮችን፣ ሰይፎችን፣ መጥረቢያዎችንና ቢላዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ ነበርና ከዝሆኑ ፊት ሁኖ ጦሩን ጭንቅላቱ ወይም ዓይኖቹ ላይ የሚወረውር ደፋር አዳኝ ያስፈልጋል፡፡

## 5

አዳኞቹ ለአደን በወጡበት ጊዜያት በከበሮው ላይ እጅግ አስፈላጊው፣ ምናልባትም ዋናው የሚባለው ሥራ- ስድስት ወራት የፈጀ ቀፎውን በተለያዩ መዓዛ ባላቸው ጢሳ ጢስ የማጠን ሥራ እየተሠራ ነበር፡፡ ምንም እንኳ ዕንጨቱ ከተቆረጠ አሁን ሦስት ዓመታን ሊደፍን ቢችልም ሥራው በዕንጨቱ ውስጥ የቀረ ርጥበት ካለ አንጠፍጥፎ ለማድረቅ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ብርካቱ ይሰጠዋል፡፡ ቀፎው እየታጠነ ውስጡም ውጬም በተለያዩ የሙጫ፣ የዘይቶችና የአጠንካሪ ፈሳሾች ውህዶች ይለቀለቃል፡፡ ከነዚህ በርካታ ፈሳሾች መካከል "ብዕሪር" እና "ቁልቋል" ከሚባሉ ተክሎች የሚዘጋጀው አንደኛው ነበር፡፡ ሂደቱ "አርስቶ" ሲሠራ እሳት ላይ የምትለቀለቀውን ዶሮ በፈሳሽ እንደመለቅለቅ ማለት ነው፡፡ እዚህ ደረጃ ላይ ነው ከፍተኛ ጥንቃቄ፣ ክትትል፣ ብስለት እንዲሁም ስለ ዕንጨቱ ደንበኛ ዕውቂያ የሚያስፈልገው፡፡ ዕንጨቱን በውህዶቹ እንደሚፈለገው ሳይቀቡ በጥድፊያና በትኩስ ጭስ ከታጠነ በቶሎ ደርቆ ሊሰነጠቅ ይችላል፡፡ በቂ ሙቀት ሳይሰጡና ጢስ ሳያጥኑ ውህዶቹን መለቅለቅ ደግሞ በዕንጨቱ ውስጥ ያለው ርጥበት እንዳይወጣ ያደርገውና ከበሮው ተጠናቆ ሲሞከር ተሰንጥቆ ያንን ሁሉ ልፋት ከንቱ ያደርገዋል፡፡ የሁለቱ ከበሮ ሠሪዎች ዕውቀትና ልምድ የሚፈተንበት ኣጋጣሚ ከዚህ ላይ ነበር፡፡ አንዴ ይህ ሥራ ከታለፈ የተቀረው ሥራ፣ ምንም እንኳ በየትኛውም መልኩ ሊናናቅ የማይችል ቢሆንም ቀላል፣ ያልተወሳሰበ፣ ቀጥተኛ አድርጎ መቁጠር ይቻላል።

አዳኞቹ ለሳምንታት ዱር ከቆዩ በኋላ ታላቅ ግዳይ ጥለው፣ ሃያ ወንዶች የተሸከሙት እንደ መሰላል በመሰለ መጫኛ ላይ የተቀመጠ ግዙፍ ቆዳ፣ እያንዳንዱ አራት አራት ሰዎች የተሸከሙት ሁለት ግዙፍ የዝሆን ጥርሶች፣ ሁለት የታፋ አጥንቶችና ስምንት የኋላ እና የፊት እግሮች አጥንቶች ይዘው ተመለሱ፡፡ አዳኞቹ እንደተናገሩት ቆዳውን በጥንቃቄ ለመግፈፍ ሦስት ቀናት ፈጅቶባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ሌላ ዝሆን ገድለው እያንዳንዳቸው በሁለት ሰዎች ሸክም የሚያዙ ጥርሶቹን ይዘዋል፡፡ የተወሰኑ አዳኞች በአደን ወቅት እግርና እጃቸውን የተጎዱ ሁለት አዳኞች ደግፈዋል፡፡ ሌሎች አራት አዳኞች ደግሞ የታዋቂውን አዳኝ፣ የነጋን አስከሬን ተሸክመዋል፡፡ ነጋ በጀግንነት በትልቅ ዛፍ ተከልሎ ዝሆኑን እየጠበቀው ነበር፡፡ የወረወረው ጦር በዝሆኑ ቀኝ ዐይን ገብቶ በግራ ዐይኑ ወጣ፡፡ ነገር ግን ነጋ በዝሆኑ እግር ተጨፍልቆ ወዲያው ሞተ፡፡ አደኑን ሲመሩት ከነበሩት ሁለት አዳኞች አንዱ ነበር፡፡ የእርሱ ሞት በ"ታላቁ ከበሮ" ዕቅድ ውስጥ የተመዘገበ ታላቅ ክስረት እርሱ ሆነ፡፡ ነጋ ለዕቅዱ ሕይወቱን አሳልፎ ሰጠ፡፡

## 6

አሁን ተራው በአገሪቱ ለሚገኙ ምርጥ ቆዳ ኣልፊዎችና ኣለሰላሾች ነው፡፡ ቆዳው ቀፎው ላይ ከመወጠሩ በፊት እንዲያዘጋጁት ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡ ቆዳው ተዘርግቶ ፀሐይ ላይ ሲወጠር ሽታው የትና የት ርቀት ድረስ ይሸት

ነበር፡፡ ጥቂት ጨው ተበትኖበት ነበር እንደተገፈፈ የተጠቀለለው፡፡ ቆዳውን የመፋቁና የማለስለሱ ሂደት ሙሉ ስድስት ወራት ፈጅቶ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ቆዳውን መሬት ላይ በዕንጨት ካስማዎች ከወጠሩት በኋላ ሁሉን ነገር በኣንድ ዝንቆላ ወደ ኣመድነት ሊለውጡ የሚችሉ ጭልፊቶች፣ ኣሞራዎችና ሌላም ኣዕዋፍን መጠበቅ ነበረባቸው፡፡ ቆዳው በጨው፣ በበሬ ሽንት፣ በኣዞ ሓሞት፣ በዘይት፣ በቅቤ እና በሌሎች ውህዶች ከተከሸነ በኋላ እንዲደርቅ ፀሐይ ላይ ለብዙ ሳምንታት ተሠጣ፡፡ ከዚያ ሽታው እስኪጠፋ ድረስና ዋና ከበሮ ሠሪዎቹ በሚፈልጉት ደረጃ እንዲለሰልስ በተለያዩ የፈሳሽ ውህዶች፣ ዘይትና ኮምጣጤ ይዘፈቃል፡፡ የኩንቢውና የእግሩ ቆዳም ለመጠፈርያ እንዲያገለግል እንዲዘጋጅ ሆኗል፡፡

ቆዳው በዕንጨቱ ቀፎው ላይ መወጠር በራሱ ቀላል ሥራ ኣይደለም፤ ምክንያቱም ምንም ዓይነት የመጨማደድ ጉርባት መኖር የለበትምና፡፡ በመጨረሻ ድምፁንና መስተጋባቱን የመሞከሪያ ጊዜ መጣ፡፡ ምርጥ ከበሮ ማስተጋባት ኣለበት፡፡ የከበሮው የዕንጨት ቀፎው ግድግዳ ውፍረት፣ የቆዳው ዝግጅት፣ የቆዳው የውጥረት ንረት የሚፈለገውን ድምፅ ከመስተጋባቱ ጋር ለማውጣት ወሳኝ ነገሮች ናቸው፡፡ ዋናው ከበሮ ሠሪ እስኪረካ ድረስ የቀፎውን ግድግዳ ከአንዳንድ ቦታዎች ላይ እስከመላግ የደረሰ በወሳኝ ነገሮች ላይ የመጨረሻ ማስተካከያዎች ተደርገው ነበር፡፡

ሆኖም ከበሮው ሊያወጣው የሚገባውን የድምፅ ጥራት በመወሰን ረገድ ግን የዋናው ከበሮ ሠሪ ፍርድ ብቻ በቂ ኣይደለም፡፡ ከበሮውን የሚመቱት፣ በተለይ የዋናው ከበሮ መቺ ቃል ወሳኝ ነበር፡፡ ከበሮ መቺዎቹ በከበሮው እስካልተደሰቱ ድረስ የዋናው ከበሮ ሠሪ ርካታ ብቻ ዋጋ የለውም፡፡ ከበሮውን ወዶት እንደሆነና እንዳልሆነ፣ በዛውም የኣመታቱን ጥበብ ሊፈትንበት የከበሮ መቺዎቹ ኣለቃ (ዋናው ከበሮ መቺ) ተጠራ፡፡ ምርጥ ከበሮ ኣምስት ድምፆችን ማውጣት ኣለበት፡፡ ምርጥ ከበሮ እንደተራሮች ማስተጋባት፣ እንደ ጉማሬ ማጉረምረም፣ እንደ ጅብ መጮኽ፣ እንደ ኣንበሳ ማጋሳት፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ እንደ ሓምሌ ነጐድጓድ ማስገምገም ኣለበት፡፡ ያለነዚህ ኣምስት ልዩ የድምፅ ቅንጅት ኣንድ ከበሮ ግሩም ከበሮ ሊሆን ይችል ይሆናል እንጅ፣ ድንቅ ከበሮ፣ ዓይነታ ከበሮ፣ ለታላቅ ንጉሥ የሚገባ ከበሮ ሊሆን ግን አይችልም፡፡

የከበሮ መቺዎቹ ኣለቃ ከዋናው ከበሮ ሠሪ ጋር ሆኖ የከበሮውን ድምፀት ሲያዳምጥ፣ የቆዳውን ውጥረት ሲያስተካክል፤ ከበሮው ጎንና ጎን በተመረጡ ቦታዎች ላይ ሲፋቅና ሲታሽ ሁለት ሳምንታትን ኣሳለፈ፡፡ ይህ ሁሉ የሚሠራው የከበሮ መቺዎቹ ኣለቃ በቋሚነት ከበሮውን እየመታ፣ የሚፈልጋቸውን ድምፅ ለማውጣት እየሞከረና በጥንቃቄ እያዳመጠ ነበር፡፡ የከበሮ መቺዎቹ ኣለቃ በመጨረሻ በእርካታ ጭንቅላቱን እስኪነቀንቅ ድረስ ሁሉም ነገር መደረግ ነበረበት፡፡

ከረጅም ቆይታ በኋላ ከበሮውን እንዲያስጌጡት ለሰዓሊዎች ተሰጠ፡፡ ስድስት ሰዓሊዎች ከኣለቃቸው ሥር ሆነው የሚያማምሩና የሚያስደምሙ ስዕሎችን መቀባት ጀመሩ፡፡ ሰዓሊዎቹ ቀለም የሚበጠብጡላቸው፣ የቀሰም ብዕር የሚያዘጋጁላቸው፣ ብሩሾቻችውን የሚያፀዱላቸው ዓስራ ኣምስት ረዳቶች ነበሯቸው፡፡ የከበሮውን ዋና ኣፍ ያስዋቡት ሁለት በግዛቱ የሚታወቁ ሰዓሊዎች ነበሩ፡፡ ንጉሡ በዙፋኑ ላይ የረጅም ዕድሜ ምልክት ከሆነው ከትልቅ የዲማ ዛፍ ሥር ተቀምጠዋል፡፡ ከንጉሡ ዳራ የሚያምር የፀሐይ ብርሃን ይታያል፡፡ ሕዝቦቹ ከንጉሡ ሥር ግብር ተቀምጠው ይበላሉ፡፡ ይህ ስዕል በግዛቱ የሰላምና ብልፅግና ዘመንን የሚያሳይ ነበር፡፡ ሌሎች ሁለት ሰዓሊዎች በትንሹ የከበሮው ኣፍ ላይ ሳሉ፡፡ የእነርሱ ስዕል ደግሞ ንጉሡ ጠላቶቹን ኣሸንፎ፣ ሠራዊቱ ድል ነስቶ፣ ምርኮ ይዘው፣ ምርኮኞች እየነዱ ሲመለሱ ያሳያል፡፡ ሁለት ተጨማሪ ሰዓሊዎች ኣበባዎችንና ተክሎችን፤ የቀሳውስትን፣ የነጋዴዎችንና የእጅ ባለሙያዎችን የዕለት ተዕለት ኑሮ እና እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም ባህላዊ ምልክቶችንና ጥልፎችን በሚያሳይ ስዕል የከበሮውን ዙሪያ ኣስጌጡት፡፡ በመጨረሻ ከበሮው ዝግጁ ሆነ፡፡ ነገር ግን ሥራው ኣልተጠናቀቀም፡፡ ከበሮውን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ መጫኛ ሠረገላ ያስፈልገዋል፡፡ የሚፈለገው ከበሮውንና መቺዎቹን ሊይዝ የሚችል በፈረስ የሚጎተት ሠረገላ ነበር፡፡

## 7

ይህ ሥራ ሲከናወን ሌሎች ጥበበኞች የዝሆኑን የታፋ፣ የፊትና የኋላ እግር ዓጥንቶች በመከሸን ተጠምደዋል፡፡ ዓጥንቶቹ መቅኔያቸው ወጥቶ ልዩ በሆነ ጨው እና ኣመድ እንዲሞሉ ከተደረገ በኋላ በሰም ታሸጉ፡፡ እነዚህ ዓጥንቶች የከበሮው መምቻ ሆኑ፡፡ ለኣያያዝም እንዲያመቹ ጭምር በሚያማምር ሁኔታ ተልገው በጠፈር ተጠለፉ፡፡ በኣጠቃላይ ጥበበኞቹ ዓስራ ሁለት ዓጥንቶችን ከሸነው ወደሚያማምሩ የከበሮ መምቻዎች ለወጡ፡፡ ኣምስት ከበሮ መችዎች ዓስሩን መምቻዎች ሲይዙ፣ ሁለት ለምናልባቱ መለዋወጫ በሚል ይቀመጣሉ፡፡

በመጨረሻም ከበሮውን የሚሸከመው ባለኣራት መንኮራኩር ሠረገላ ተሠራ፡፡ ሠረገላው ኣራት ከበሮ መችዎች ቆመው እንዲጫወቱ የሚበቃ ነበር፡፡ መወጣጫ ዕንጨቶች ከመሬት ወደ ሠረገላው ካጋደሙ በኋላ ከበሮውን እየፈሩ እየቸሩ በጥንቃቄ ጎትተው ጋሪው ላይ ኣወጡት፡፡ ምንም እንኳ ከበሮው መጀመሪያ የግንድ ጉማጅ ከነበረበት መጠኑ አሁን የቀረው የቀፎ ያህል ኣንሶ ክብደቱ ቀላል ቢሆንም፣ ኣራት ፈረሶች የሚጎትቱት ሠረገላ እና ሠረገላው ላይ ጎትቶ ለመጫን ሃያ ኣራት ሰዎች ያስፈለጉት ግዙፍ ነበር፡፡ ከበሮው እንዳይንቀሳቀስ በኣራት ችካሎች ከወጠሩት በኋላ እንዳይንከባለል ከዝሆኑ ኩንቢ እና እግር ቆዳ በተዘጋጁት ጠፍሮች ከሠረገላው ጋር ኣሰሩት፡፡ እንደ ውበት እንዲያገለግል የዝሆኑን ጥርሶች ቅስት-ድልድይ ኣስመስለው ሠረገላው ላይ ከከበሮው ግራና ቀኙ ጎኑ ኣስቀመጡ፡፡ ልክ ይህ ሲያልቅ የ"ታላቁ ከበሮ" ዕቅድ እንደተጠናቀቀ ተበሠረ፡፡ የንጉሡ መልእክተኛም የከበሮው መጠናቀቅ እና ወደ መሃል ኣገር ጉዞ የመጀመሩን መልካም ብስራት ለንጉሡ እንዲነግረው ተላከ፡፡ አሁን በወቅቱ የኢትዮጲያ ዋና ከተማ እና መንበረ ንግሥ ወደ ሆነችው ኣክሱም የሚደረገው ረጅም ጉዞ ተጀመረ፡፡ ሁሉንም ድንኳኖች መንቀልና ጎጆዎችን ማፍረስ ኣለባቸው፡፡ ነገር ግን በኣካባቢው ቋሚ መንደር ተመሥርቶ ስለነበር የተወሰኑ ሰዎች በዚያው መቅረት መረጡ፡፡

## 8

**ጉዞ ወደ ቤት፡** ላለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት በጊቤ ወንዝ ዳርቻ በድንኳን ከትሞ የነበረው የሠራተኞችና የወታደሮች ሠራዊት ኣሁን ደግሞ እንደ ኣዲስ ተለውጦ የ"መሃንዲስ" ሠራዊት ሆኗል፡፡ በኣስፈላጊ ቦታዎች ሁሉ መንገድ ቀድመው ይጠርጋሉ፣ ቋጥኝና ዓለቶችን ይፈነቅላሉ፣ ጉድጓዶችን ይሞላሉ፣ ቁጥቋጦችን ይመነጥራሉ፡፡ ምግብ የሚያዘጋጁት እና ውሃ የሚያመጡት እንዲሁም ሌሎች ጋሻ ጃግሬዎች ብቻ ናቸው በቀድሞው ሥራቸው ላይ የቆዩት፡፡ ሁለት እንስሳ ጐን-ለጐን ሊያሳልፍ የሚችል መንገድ ነበር ከሠረገላው ፊት ፊት የሚጠረገው፡፡ ሠረገላውን ለመጎተት በቋሚነት ከተዘጋጁት የጋማ ከብቶች ኣንዳንድ ጊዜ ፈረሶች ሌላ ጊዜ ደግሞ በቅሎዎች ኣገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ኮረብታዎችንና ተራራዎችን ጭምር ማለፍ ነበረባቸውና ሠረገላው ኣክሱም ለመድረስ ስድስት ወራት ፈጅተውበታል ማለት ይቻላል፡፡ ከበሮውን ከግዛቱ ጋር ያስተዋወቀው ጉዞ ይህ ነበር፡፡

ንጉሡ ራሱ የመረጣቸው ዓስራ ኣምስት ምርጥ ከበሮ መችዎች ኣምስት ኣምስት ሆነው በሦስት ቡድኖች ተከፍለዋል፡፡ ሁሉም በዋናው ከበሮ መች ይመራሉ፡፡ እያንዳንዱ ቡድን ሁለት ረጃጅም፣ ፈርጣማ እና ግዙፍ፣ ሁለት መካከለኛ ቁመት ያላቸውና ኣንድ ድንክ ኣባላትን ያካተተ ነበር፡፡ ሁሉም ከበሮ መችዎች ሕይወታቸውን በሙሉ ከበሮ ሲመቱ የኖሩ በመሆናቸው ሁሉንም ምቶች ከነምጣኔዎቻቸውና የዜማ ቅንብር ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ለዚህ ኣስተማማኝ ማረጋገጫ የሚሆነው ሁሉም በከፊል ኣሊያም ሙሉ ለሙሉ ደንቁረዋል፤ ከበሮ መችዎች የሰላ የመስማት ችሎታ እንደሌላቸው የሚታወቅ ነገር ቢሆንም፣ ኣንድ ከበሮ መች የሚያስፈልገው ነገር ከእጅ ጣቱ እስከ እግሩ ኣውራ ጣት ጫፍ፣ መላ

ሰውነቱ የተዋሃደው የጊዜ አጠባበቅና የምጣኔ ችሎታ ማዳበር ብቻ ነው፡፡ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ሁሉም ቡድኖች ተዋህደው በአንድነት ለሰዓታት ሳያቋርጡ መጫወትና ትርዒት ማሳየት ችለዋል፡፡

ከዝሆኑ የታፋ ዓጥንቶች የተዘጋጁት መምቻዎች የተሰጡት ለረጅሞቹ ሲሆን ከከበሮው ዋና አፍ ጎንና ጎን ቆመው ይጫወታሉ፡፡ እያንዳንዳቸው እነዚህን ግዙፍ መምቻዎች በቀኝ እጃቸው፣ በግራ እጃቸው ደግሞ ቀለል ያሉትን ከዝሆኑ የፊተኛ እግሮቹ የተዘጋጁትን ረጃጅም መምቻዎች ይይዛሉ፡፡ ሁለቱም መችዎች የፊትና የኋላ ገላቸውን ለመሸፈን ብቻ ሙሉ ለሙሉ ከነብር ቆዳ የተዘጋጀ ልብስ ሲለብሱ ቀኝ እጃቸውና ትከሻቸው ሙሉ ለሙሉ ተራቁቷል፡፡ ግንባሮቻውም ላይ የአንበሳ ጎፈር አስረዋል፡፡ ሁለቱ ባለ መካከለኛ ቁመታሞቹ በሠረገላው የኋለኛ ክፍል፣ በከበሮው አነስተኛ አፍ ዳርና ዳር ሆነው ይቆማሉ፡፡ ከዝሆኑ የፊት እግር ዓጥንቶች የተዘጋጁትን ረጃጅም መምቻዎች ሲይዙ እንደ መደበኛ እግረኛ ወታደር ለብሰዋል፡፡

በመጨረሻም በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ያለው ድንክ ከረጃጅሞቹ መችዎች ከፍ ብሎ እግሩን አንፈራጥጦ በከበሮው ላይ ይቀመጣል፡፡ የጉሬዛ ወይም የጭላዳ ዝንጀሮ ቆዳ የሚለብስ ሲሆን፣ የጥቁርና ነጭ ፀጉር ቆዳ ከታች ሲለብስ ደማቅ ቀይ ሻሽ ራሱ ላይ ያስራል፡፡ በእጁም ከኋለኛው የዝሆን ዓጥንት የተዘጋጀውን ወፍራም እና ከበድ ያለውን መምቻ ይይዛል፡፡ አምስት አባላት ያሉት የከበሮ መችዎቹ ቡድን ይህንን ይመስላል፡፡

## 9

ሦስቱ ቡድኖች የሚጫወቱት ተራ በተራ ነበር፡፡ የመጀመሪያው ቡድን ማለዳ ላይ ጉዞ ሲጀመር ጀምሮ ለሦስት ወይም ኣራት ሰዓታት ከተጫወተ በኋላ ረፋድ ላይ፣ ፀሐይዋ መጋል ስትጀምር ያቆማል፡፡ ለሃያ ወይም ሠላሳ ደቂቃዎች ከታረፈ በኋላ ሁለተኛው ቡድን እስከ ተሲያት በኋላ ይጫወታል፤ የፀሐይዋ ንዳድ የማይቻል ሲሆን ያቆማል፡፡ ሦስተኛው ቡድን ይቀጥልና እስከ ኣመሻሽ፣ ለኣዳር እስኪሰፍሩ ድረስ ይጫወታል፡፡ ከበሮ መችዎቹ የተለያዩ ዜማዎችን ነበር የሚጫወቱት፡፡ ኣንዳንዴ ለስላሳና ቀዝቀዝ ያለ፣ ልክ እንደ ቤተ-ክርስትያን የንግሥ በዓላት ጊዜ እንደሚመታው ምት ይመታሉ፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሞቅ፣ ፈጠን ፈጠን ብለው እየሙቱ ይጫወታሉ፡፡ ሁለቱ ረጃጅሞቹ ከበሮ መችዎች በሙሉ ኃይላቸው ከበሮውን ሲደልቁት ምድሯ ታረገርግ ነበር፡፡ የማንንም ልብ ያርዳል፡፡ ልክ እንደ መሬት መንቀጥቀጥ ዓይነት ስሜት ነበረው፡፡ እስከ ሰማንያ ኪሎ ሜትሮች፣ ከዚያም በላይ ርቀት ያሉ ሰዎች ያደምጡታል፡፡

እነዚህ ውስጥ ድረስ ዘልቀው የሚሠሙ ምቶች እና ሰዎች የ"ንጉሡ ከበሮ" እያሉ መጥራት የጀመሩት የከበሮው ዝና በሙቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ከያሉበት እያሰባሰበ በሚያልፍበት መንገድ ዳርና ዳር ያሰልፍ ነበር፡፡ ከበሮው ተኣምራዊ ኃይል እንዳለው በሰዎች ዘንድ መናፈስ ጀመረ፡፡ ሰዎች ከበሮውን ወይም የተሸከመውን ሠረገላ ለመንካት እና ለማየት ከሩቅ መንገድ ተጉዘው ይመጡ ነበር፡፡ ኣንዳንዶች ከበሮው ርኩስ መናፍስትን ያስለቅቃል ሲሉ ሌሎች ደግሞ ሰውን ጥበበኛና ብልህ የሚያደርግ ኃይል ኣለው ይላሉ፡፡ ነፍሰ ጡር ሴት ከበሮውን ከነካችው የተረገዘው ልጅ ታላቅ መሪ ይሆናል ያሉም ነበሩ፡፡ ከበሮውን መንካት ብቻ መልካም ዕድል ያስገኛል የሚሉም ነበሩ፡፡ ምን ተባለ ምን ከበሮው በሕይወት ዘመን ለኣንድያ የሚታደሉት ኣጋጣሚ ነበር፡፡ ከበሮው ከዚያ በኋላ በዚያ መንገድ ኣያልፍም፡፡ ያዩት ሁሉ በግዙፍነቱና በኃይሉ ተደንቀዋል፡፡ ከከበሮው ጨዋታ ጋር ኣብረው እየጨፈሩ፣ ከበሮ መችዎቹ ሲጫወቱ ፊታቸውን እያጠበ የሚወርደውን ላቦት፣ በላቦቱ የወረዛውን ኣንፀባራቂ ገላ እየተመለከቱ ለሰዓታ ሠረገላውን ተከትለው ይጓዛሉ፡፡ ገበሬዎቹ እርስ በርሳቸው ሊሉት እንደሚችሉት "ከበሮ መደለቅ በርግጥ ኣድካሚ ነገር ነው፡፡" ቀኑን ሙሉ ስንለፋ

ብንውልም እንደዚህ ፋታ ኣጥተን ላባችን ጠፍ ኣይልም፡፡ ሲደክመንም በእርሻና በሜዳዎቻችን ዐረፍ ማለት እንችላለን፡፡ ከበሮ መችዎቹ ግን ሳያቋርጡ መምታት ኣለባቸው፤ ሙሉ ለሙሉ ድስቅ ብለው ቢደክሙም ትርዒቱን ማቋረጥ ኣይችሉም፡፡ ትርዒቱ ካላለቀ ከበሮ መችው ዕረፍት የለውም፡፡ ደግሞም ቀን ተቀን መጫወት ኣለባቸው! "ጭሰኛ ሆኖ ኣፈር መግፋት ይሻላል። ሕይወታችን ከባድ ናት ብለን እናስብ ነበር፣ የከበሮ መች ሕይወት ግን ከኛ ሕይወት እጅግ የከበደች ናት" ሳይሉ ኣልቀሩም፡፡

የሴቶቹ ኣመለካከት ግን ፈፅሞ የተለየ ነበር፡፡ በላቦት የወረዛውና ኣንፀባራቂ የከበሮ መችዎቹ ገላ እጅግ ማራኪና ፍቅር ቀስቃሽ ሆኖባቸዋል፡፡ ከበሮው ባለፈባቸው ቦታዎች ሁሉ ሴቶች በከበሮ መችዎቹ ተማርከው ያንጎራጎሯቸው ዜማዎች መደመጥ የተጀመሩት ወዲያውኑ ነበር፡፡

ከበሮ መቺ ሆይ ውሰደኝ ካንተ ጋር

በቃህል "ነዪ!" በለኝ፣ ኣሊያም በጥቅሻ

ጓደኞቼን ሳልሰናበት፣ እናት አባቴን

እከተልሃለሁ ወጥቼ ብቻዬን

ይህችን የደረብኳት ነጠላ ለብሼ

እመጣለሁ ኣኮሱም ጥርሴንም ነክሼ

የቅማላም ገበሬ ሚስትስ ከመሆን

መወሽም ይሻላል ከበሮ መችን

ሌላው ዜማ የሚከተለው ይዘት ነበረው፦

ከበሮ መቺው ልቤን መውሰዱ ምን ያጠራጥራል?

ሰው ሁሉ እሚያውቀውን ምን መጠየቅ ያሻል?

ይልቅስ ሚስቲቱን ጠይቁልኝ በሰው

ባሏ ልቤን ወስዶ ወዴት ኣደረሰው!

የከበሮው ቡድን ለሚያቀርቡት ትርዒት ገበሬዎች ምግብ እንዲያቀርቡና የሚጠጣ እንዲሰጧቸው ንጉሡ እንዳዘዘ ተሰምቷል፡፡ የኢትዮጲያውያኖች ከቆየ እንግዳ ተቀባይነት ባህላቸው ጋር ገበሬዎቹ የንጉሡን ትዕዛዝ የተቀበሉት በደስታ ነበር፡፡ ለቡድኑ በሙሉ፣ በተለይ ለከበሮ መችዎቹ የበሰለ ምግብ፣ ፍራፍሬዎች፣ ወተት እና ሌሎች መጠጦች እንዲሁም ምግብ ማንሸራሸሪያዎች በገፍ ይዘው መጡ፡፡ ተጓዥ መንገደኛንና እንግዳን ውለታ ሳይቆጥሩ ማስተናገድ ቀድሞ እንደነበረ ሁሉ ኣሁንም ድረስ ያለ ባህል ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ እንግዶች ብቻ ኣይደሉም፡፡ ልባቸውን የሰረቁ፣ ያዝናኗቸው፣ ያስደመሟቸው ከበሮ መችዎች ናቸው፡፡ ተራ ከበሮ መችዎችም ኣይደሉም፣ የንጉሡ ከበሮ መችዎች

ናቸው፡፡ ምግብ ያማያመጡና ሊያመጡ ያልቻሉት ለሁለት ሰዓታት ያህል የጉልበት ሥራ ይሠራሉ፡፡ በመንገድ ጠረጋው፣ ኣፈርና ደንጋይ በማመላለሱ፣ በቁፋሮውና ለመሸጋገሪያ የሚሆን ግንድ በማንጠፍ ያግዛሉ፡፡ የንጉሡ ከበሮ በመንደራቸው ሲያልፍ ለማየት ለመጣ ሁሉ ኣስደሳችና የማይረሳ ኣጋጣሚ ነበር፡፡ ይህ ወቅታዊና እየተሠራ ያለ ታሪክ ነበርና ሁሉም ሰው በተቻለው መሳተፍ በመቻሉ ራሱን እንደ ዕድለኛ ቆጥሮታል፡፡

**10**

ከበሮው ወደ ኣክሱም ከተማ ዳርቻ እየተቃረበ ሲመጣ ኣቀባበል ሊያደርግለት ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ ከገበያው ቦታ ተሰባሰበ፡፡ የከተማው ሰው የከበሮውን ድምፅ መስማት ከጀመረ ከዛሬው ጭምር ሦስት ቀናት ሆኗል፡፡ ከመንገዱ ኣለመመቸትና ከከበሮው ክብደት ሠረገላውን የሚጎትቱት ፈረሶች ሊጋልቡም ሆነ ሊያሰግሩ ኣልቻሉም፡፡ ኣድካሚ በሆነ ሁኔታ ቀስ እያሉ በመራመድ የሚጓዙት በቀን ዓስር ኪሎ ሜትሮች ግፋ ቢል ከዚያ ትንሽ ቢያልፍ ነው፡፡

ረፋዱ ላይ የከበሮው ጓዝ ፊተኞቹ ከኣድማሱ ባሻገር በደብዛዛው መታየት ሲጀምር በሊቀ ጳጳሱና ንቡረ-ዕዱ የሚመራ የቀሳውስት ስብስብ ባማረ የቤተ ክርስትያን ኣልባሳት ተንቆጥቁጠው፣ እጅግ በሚያማምሩ ዣንጥላዎችና ድባቦች ሥር ፅላተ ሙሴን ይዘው ወደ ገበያው ቦታ ወርደው የከተማይቱን ማዕከላዊ ቦታ ያዙ፡፡ የማዕበሉ ድምፅ ግምግምታ በየደቂቃው እየቀረበ ቢሆንም ከበሮውና የተሸከመው ባለኣራት ፈረስ ሠረገላ እስኪደርሱ ሕዝቡ ለኣራት ተጨማሪ ሰዓታት፣ እስከ ተሲያት፣ ፀሐይዋ ግርር እስክትል መጠበቅ ነበረባቸው፡፡

በመጨረሻ ሠረገላው በፈረሶቹ እየተጎተተ፣ ከበሮ መቾዎቹ ከበሮውን እየነረቱት ደረሱ፡፡ ቡህ ቡህ፣ ትርም ትርም፣ ዋህ ዋህ፣ ቡም ቡም፣ ትዝም ትዝም፣ ቡህ ቡህ፣ ትርም ትርም፣ ዋህ ዋህ፣ ቡም ቡም፣ ትዝም ትዝም... ታሪኩን ካቀበሉኝ ሰዎች ያሰሙኝ የከበሮው ድምፅ ኣንጻር በተቻለ መጠን በቃላት ለማቅረብ የቻልኩት እንደዚህ ነው፡፡ ከነዚህ ኣምስቱ ዋና ዋና ድምፆች መካከል በተጨማሪ በተለያዩ ደረጃዎች የሚሰሙ ድምፆች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ የ“ቡም ቡም” ድምፀት ከሹክሹክታ ጀምሮ የመብረቅ ቁጣ እስኪመስል ድረስ ሊመታ ይችላል፡፡ የተቀሩትም ድምፆች በእንደዚሁ የተለያዩ ደረጃዎች ሊመቱ ይችላሉ፡፡ በእነዚህ ድምፀቶች ቅንብር የሚሰማው ዜማ ኣዝናኝ ከመሆኑ የተነሳ ቀኑን ሙሉ ሲደመጥ ቢውል የሚሰለች ኣልነበረም፡፡

የከተማው ሰው እና ቀሳውስቱ በከበሮው ነጐድጓዳ ድምፅ ርዷል፡፡ የቆሙባት መሬት ከእግራቸው ስር ስትርገበገብ በታላቅ ኣድናቆት ተውጠው ነበር፡፡ ሠረገላው የገበያውን ቦታ ለሦስት ጊዜያት ከዞረ በኋላ ፅላተ ሙሴው እና ሊቀ ጳጳሱ ከተከታዮቻቸው ከተሰየሙበት ቦታ ብዙም ሳይርቅ ቆመ፡፡ ከበሮ መቾዎቹ ንጉሡ እስኪመጣ ድረስ ለኣንድ ሰዓት ያህል ሲጫወቱ ቆይተዋል፡፡ ንጉሡ በነጭ ፈረሱ ተቀምጦ ወደ ኣንድ ደርዘን ከሚሆኑ ራሶቹና ደጃዝማቾቹ ጋር እየጋለቡ መጡ፡፡ ሌሎች በርካታ ከፍተኛ ሹማምንትና ባለስልጣናት የተወሰኑት በፈረስ እየጋለቡ የተቀሩት ደግሞ በእግራቸው በሶምሶማ እየሮጡ ራሶቹንና ደጃዝማቾቹን ተከትለዋል፡፡ ንጉሡ ከፈረሱ ወርዶ ከቀሳውስቱ በስተቀኝ በኩል ከከበሮው ፊት ለፊት ካለው ቦታ ተሰየመ፡፡ ኣሁን ወደዚህ ድንቅ ከበሮ የተለወጠውን ግዙፍ ጉማጅ ግንድ ለመጀመሪያ በጊቤ ወንዝ ዳርቻ ተጋድሞ ካየው ሦስት ዓመታት ኣልፎታል፡፡ የሥራውን ሂደት ሁሉ በመልእክተኞቹ በኩል ከሠራተኞቹ ጋር በቅርበት ሲከታተል ነበር፡፡ ስለዝርዝር ሥራውና ሂደቱ ሙሉ መረጃ ኣለው፡፡ ሆኖም ኣሁን በሚያየው ነገር ተደንቋል፡፡

ንጉሡ ወደ ከበሮው አምርቶ በጥንቃቄ አሠራሩን መረመረ፣ የተሳሉትን ስዕሎች ተመለከተ፡፡ በጣም ድንቅ ነበር፡፡ ሁለቱን ዋና ከበሮ ሠሪዎች ጠራቸው፡፡ ተንደርድረው እግሩ ሥር ወደቁ፡፡ በእጆች አንስቷቸው በደስታ ተቀብሎ አቀፋቸው፡፡ በእርግጥ ይህ አንድ የጥበበ ባለሞያ በቀላሉ የሚያገኘው ክብር አልነበረም፡፡ በዚያው ቅፅበት ሁለቱም ጠረኞች ባይሆኑም የክብር ደጃዝማችነት ማዕረግ ተሰጣቸው፡፡ የአዳኞቹን አለቃ መሪ ጠራው፡፡ ወደፊት ቀረበ፤ የደጃዝማችነት ክብር ተሰጠው፡፡ ከዚያ ንጉሡ በአደኑ ወቅት ሕይወቱ ያለፈችውን የጀግናውንና የደፋሩን አዳኝ የነጋን ስም አውስቶ ለክብሩ ሲል ታላቁን ከበሮ "ደጃች ነጋ" ሲል ሰየመው፡፡ በዚህ ዕውቅና የነጋ ቤተሰቦች የመሬት ባላባትነት ጥቅም እንደሚያገኙ ጥርጥር የለውም፡፡ በመቀጠል ከበሮውን በስዕል ያሸበረቁትን ሰዓሊዎች ከነአለቃቸው ጠራ፤ ሁሉም የ"ብላታ"ነት ማዕረግ ሲሰጣው አለቃቸው ብላቴን ጌታ ተባለ፡፡ ላለፉት ዓመታት የካምፑን ሠራተኞች ከጠላትና ከአውሬ ጥቃት በታላቅ ተጋድሎ ሲጠብቁ የነበሩትን ወታደሮች ጠራ፡፡ የመሬት ርስትና በጦሩ ውስጥ የደረጃ ዕድገት ሠጣቸው፡፡ ንጉሡ ይህን ሁሉ ካበቃ በኋላ ሥነ ስርዓቱ እንዲጀመር የመክፈቻ ቡራኬ እንዲያቀርቡ ወደ ሊቀ ጳጳሱና ንቡረ-ዕዱ ፊቱን አዙሮ ምልክት ሰጣቸው፡፡

**የመክፈቻ ሥነ ስርዓት፣ "ቡራኬው"**

ተራው የቀሳውስቱ ሆነ፡፡ ሊቀ ጳጳሱ ወደፊት ሲጠጉ ንቡረ ዕዱ፣ አቡኖቹና እጨጌዎቹ- ባጠቃላይ ወደ  ዓስራ ሁለት የሚሆኑ ጥቁር አልባሳታቸውን ለብሰው፣ ከፍ ያለው ባለ ደርዝ ኮፍያቸውን እንዳጠለቁ ተከተሏቸው፡፡ በግዕዝኛ ለስለስ ብሎ በግልፅ የማይሰማ ረጅም ፀሎት በማጉተምተም ጀመሩ፡፡ የገበያው ቦታ በፍጹም ፀጥታ ተዋጠ፡፡ በሃር ጨርቅ የተጠቀለለ የወርቅ መስቀል የያዙበትን ቀኝ እጃቸውን አንስተው ወደ ከበሮው እንደጠቆሙ የመስቀል ምልክት አመላከቱ፡፡ ይህን ለሦስት ጊዜያት አደረጉ፡፡ አንደኛው ቄስ ወደፊት ቀረብ ብሎ ፀበል የያዘ የብር ፅዋ አቀረበላቸው፡፡ አቡኑ እጃቸውን በፅዋው ውስጥ ከነከሩ በኋላ መጀመሪያ ጸበሉን ወደ ንጉሡ አቅጣጫ ፈነጠቁ፡፡ ከዚያ ቀሳውስቱ እየተከተሏቸው ሠረገላውና አራቱ ፈረሶች ላይ በግዕዝ ቃለ ቡራኬ እያሰሙ ለሦስት ጊዜያት እየዞሩ ጸበል ረጨዋቸው፡፡ አንዱም አቡን እርሳቸውን እየተከተለ ጥናውን ወደግራና ቀኝ እያወራጨ ዕጣን ያጥናል፡፡ ከበሮው የሰላም፣ የብልፅግና እንዲሆን ንጉሡም የንግሥናው ዘመን እንዲረዝም ተመኙ፡፡

ሊቀ ጳጳሱና አቡኖቹ ጸሎታቸውንና ቡራኬያቸውን ሲጨርሱ በቦታው ቀሳውስቱ ተተኩ፡፡ ለበዓሉ ተዘጋጅተዋል፡፡ ነጭ ካባ ደርበዋል፣ ነጭ ጥምጣም ጠምጥመዋል፣ በአንድ እጃቸው መቋሚያ በሌላ እጃቸው ፀናፅል ይዘዋል፡፡ ፅላተ ሙሴውን የያዙት በሚያማምሩ ዣንጥላዎቻቸው ጥላ ሥር እንደቆሙ ታላቁን ከበሮ ሦስት ጊዜ ዞሩት፡፡ ከዚያ ፅላተ ሙሴውን የያዙት ገለል ሲሉ ቀሳውስቱ በሦስት ረድፍ ሆነው ሠረገላውን በአራቱም መዓዘን ከበቡት፡፡ በአንድነት ወደ ቀኝና ግራ እያሸበሸቡ፣ ወደ ፊትና ኋላ እያረገዱ፣ ፀናፅሎቻቸውን እያንሹዋሹ፣ መቋሚያቸውን ወደ ላይ ከፍ ሲያደርጉ አብረው ድምፃቸውን ከፍ እያደረጉ፣ እንቅስቃሴያቸውና ዜማቸው እስኪቀልጥ ድረስ ቆዩ፡፡ ይህ ቅዳሴ፣ አቋቋም፣ ማህሌት ወ.ዘ.ተ. ከሚባሉት የቤተ ክርስትያን ሥነ ስርዐት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ሁሉም በደስታ ስሜት ተውጦ ነበር፡፡ ሥነ ስርዓቱ ፀሐይ እስክትጠልቅ ድረስ ለሁለት ሰዓታት ሙሉ የሚሆን ቀጠለ፡፡

በመጨረሻ ሽብሸባውና ዜማው ሲጠቃለል ሊቀ ጳጳሱ ቀርበው የማሳረጊያ ፀሎት አደረሱ፡፡ አሁንም መርፌ ብትወድቅ እንኳ እስክትሰማ ድረስ የገበያው ቦታ በፍጹም ጸጥታ ተዋጠ፡፡ ፀሎቱ ሲፈፀም ሰዉ ተበተነ፡፡ ንጉሡም ፈረሱ ላይ ወጥቶ ወደ ቤተ መንግሥቱ አመራ፡፡ ሠረገላውና ከበሮ መችዎቹ ከበሮውን በታላቅ ደስታ እየሙቱ ተከተሉት፡፡

ያን ምሽት በቤተ መንግሥቱ በከበሮው ሥራ ላይ ለተሳተፉት ታላቅ ድግስ ተደገሰ፡፡ ሁለቱ ባለሙያዎች ክብር ኣግኝተው ከእውነተኞቹ ጦረኛ ደጃዝማቾች እኩል ቀርበው ከንጉሡ ማዕድ በሉ፡፡ ከእራት በኋላ ንጉሡና እንግዶቹ በቤተ መንግሥቱ ሰገነት ላይ ሲሰየሙ ከበሮ መችዎቹ ትርዒታውን ቀጠሉ፡፡ እስከ ሌሊት ድረስ ቆዩ፡፡ የከተማው ሰው ከበሮው ከሚያወጣው የተለያዩ የምት ድምዖች እና ትርጉማቸው ጋር እስኪላመድ ድረስ ለበርካታ ተከታታይ ሌሊቶች ትርዒቶች ተከናወኑ፡፡ የደስታና ፈንጠዝያ ምት፣ የማስጠንቀቂያ ምት፣ ኣዋጅ ከመነገሩ በፊት የሚመታ የ“ጸጥ በሉ” ምት፣ የ“ልብ አድርጉ” ምት፣ “ለጦርነት ክተቱ” ምት፣ ጠላትን ለማሸበር የጉማሬ ጉርምርምታ ምት እና ሌሎች የተለያዩ ትርጉሞች ያሏቸው ምቶች ነበሩ፡፡ ኣድማጩን ከማስደሰት ውጭ ትርጉም የሌላቸው ምቶችም ይመቱ ነበር፡፡

ታላቁ ከበሮ ለንጉሡና ንግሥናውን ለተረከቡት ሁሉ ዋጋ የማይገኝለት ውድ ንብረት ሆነ፡፡ በዋና ዋና ክስተቶችና መንግሥታዊ በዓላት ሁሉ ተደምጧል፡፡ ከእያንዳንዱ ኣገልግሎቱ በኋላ ከበሮው ይፀዳል፣ ይወለወላል፤ የረገበውም ይወጠራል፡፡ ለሚቀጥለው ኣገልግሎት ዝግጁ ሆኖ ለመኖሪያው ተብሎ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ በተዘጋጀለት ቤት ይቀመጥ ነበር፡፡ ይህ ከበሮ ከኣንዱ ንጉሥ ወደ ሌላው፣ ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ ለበርካታ ዓመታት እንደቆየ ተነግሮናል፡፡ ዛሬ የት እንዳለ ግን የሚያውቅ የለም፡፡ ሦስቱ የታሪክ ኣቀባዮቻችን በሰፊው የሚለያዩት ከዚህ ላይ ነው፡፡

ከሁለቱ ወንድ ታሪክ ኣቀባዮቻችን ኣንዱ በኣፄ ቴዎድሮስ ሞት ጊዜ የሮበርት ናፒር ጦር የመቅደላን ምሽግ ሰብሮ ሲዘርፍ ወደ እንግሊዝ ኣገር ወስደውት ይሆናል ብሎ ይጠረጥራል፡፡ ሌላው ከበሮው እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ ለረጅም ዓመታት ቆይቷል፤ ፋሽስት ከኣኩሱም ሓውልት ጋር ሰርቀው ወደ ሮም ወስደውታል ብሏል፡፡ ነገር ግን ሴት ታሪክ ኣቀባያችን ከበሮው የተሰወረው ከነዚህ ጊዜያት በፊት እጅግ ቀደም ብሎ በኣሕመድ ግራኝ ዘመን ነው ትላለች፡፡ ምናልባትም ግራኝ በእሳት ኣውድሞት ወይም ለቱርክና ለዓረብ ደጋፊዎቹ በስጦታ መልክ ኣበርክቶት ይሆናል ብላለች፡፡

ይህች ሴት ሌላ የነገረችን ኣስገራሚ ታሪክ ‘ነጋሪት’ የሚለው ቃል በእርግጥ ከዚህ ከበሮ ጋር ተያይዞ የመጣ መሆኑን ነው፡፡ ሰዎች ንጉሡ ለሟቹ ኣዳኝ ክብር ሲል ከበሮው “ደጃች ነጋ” ተብሎ እንዲጠራ ባዘዘው ስሙ ሲጠሩት ነበር፡፡ ለብዙ ዓመታት በዚህ ስም ሲጠቀሙ ከቆዩ በኋላ ስሙ ለኣጠራር ስለረዘምባቸው ‘ነጋ’ ብቻ ብለው መጥራት ጀመሩ፡፡ ከዚያ ከበሮው “ተናጋሪ” በመሆኑ በኣጭሩ “ነጋ-ሪት” አሉት፡፡

ዛሬ የቀሩን ሁለት ነገሮች ናቸው፡- ይህ ኣፈ ታሪክና ከከበሮው ጋር በተያያዘ የመምጣቱ ነገር እውነት ሊሆን ወይም ላይሆን የሚችለው ‘ነጋሪት’ የሚለው ቃል፡፡ ልዩነቶችን ወደጎን ትተን ይህ ኣፈ ታሪክ በእውነት ላይ የመመስረቱ ነገር ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በበቂ ሁኔታ በጥንቃቄ ጥናት እስካልተደረገ ድረስ የዚህ ታላቅ ከበሮ ታሪክ የመጨረሻው ምዕራፍ ሊጻፍ ኣይችልም፡፡

*ገ/ኢ. ጐርፉ፣ ሎስ አንጀልስ (ጥቅምት 1989)*